ሙክታር - ምን ማለትህ ነው? - ምንድነው እሱ?

ቲሞቲ - ሙክታር! ስለጠጣህ ምን እንደሠራህ ረስተናል?

- ባለፈው ምሽት ሴተኛ አዳሪ ይዘህ ወደ ቤርጎ ገብተሃል

- ራስህን እንድትከላከል ይህን ኪስህ ውስጥ ከትቼ ነበር ለአይቻም ጭምር!

ሙክታር - አምላኬ! እኔ አላምንም!

- አገኘሁት! ተይዣለሁ:: ይህም የእኔ ጥፋት ነው

ቲሞቲ - አዳምጥ! እርሷ ወይም አንተ መያዛችሁ እርግጠኛ መሆን አይቻልም:: በሦስት ወር ጊዜ በሚካሄደው በኤች.አይ.ቪ. ደም ምርመራ ብቻ ነው የሚታወቀው ተመርምረህ ተገኝቶብሃል ከተባለም እኔ ካንተ አልለይም ጓደኛዬ:: አሁን ግን እርግጠኛ እስከትሆን ድረስ ወደ አይቻ እንዳይዛመት ተከላከል፡፡

ሙክታር - ወደ እሷ የማስተላልፍበት ምንም ጉዳይ የለኝም፡፡ ግን እንዴት እነግራታለሁ::

*******

## ገቢር አስራ ሶስት

<u>ተዋጊው</u>

እናት - ልጄ! የት እየሄድክ ነው?

ተዋጊው - ኤድስን ልዋጋ መሄዴ ነው እናቴ፡፡ ያለምንም ፋታ ወንድሞቼን እና እህቶቼን እያጠፋ ነው ስለዚህ ጦርነት ላውጅበት ነው የምሄደው

ተዋጊው - ና ውጣ! ኤድስ ወዲህ ና የት ነው ያለኸው?

ፖሊስ (ወንድ) - እዚያ ቁም!

ተዋጊው - ሄይ ኤድስ ኤድስን እየፈለግሁት ነው የት ነው የተደበቀው?

ፖሊስ (ወንድ) - እብድ ነህ? ሂድ! ሂድ ከዚህ! ሞኝ

ተዋጊው - መግደል እንድችል ኤድስን እየፈለግሁት ነው

- ሄይ! ወይዘሪት

ልጃገረድ - እሺ! ምን ትፈልጋለህ?

ተዋጊው - ቆንጆ ነሽ! በጣም ቆንጆ!

ልጃገረድ - ገንዘብ አለህ?

ተዋጊው - ገንዘብ ነው! ያው እዩ

ልጃገረድ - ይህ ብቻ ነው! በጣም ብዙ አይደለም::

- እሺ! የፍቅር ጓንት አለህ?

ተዋጊው - ዓንት? ኖ! ግን በጣም ጥሩ የሆነ ጎጆ አግኝቻለሁ::

ልጃገረድ - ሞኝ አትሁን! አዳምጥ፤ ኮንዶም ካልያዝክ ካንተ ጋር አልሄድም፡፡ ኤድስ እንዲይዘኝ አልፈልግም::

ተዋጊው - ኤድስ የታለ? ጉዱን ነው የማፈላው

ልጃገረድ - አትረዳም? ቫይረስ ነው እኮ! አንተም ውስጥ እኔም ውስጥ ሊኖር ይችላል ከምትዋጋበት መንገድ መካከል አንዱ ይህንን ማወቅ ነው እሺ

## ተፈፀመ